# የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የጀርመን ቅርንጫፍ።

**ETHIOPIAN PEOPLE REVOLUTIONARY PARTY (EPRP)**
**<u>GERMAN SECTION</u>**

**POSTFACH 511213, 13405 BERLIN**

**10.05.2007**

## የአቋም መግለጫ

የጀርመን ኢሕአፓ አገራዊ ኮሚቴ በአፕሪል 28 እና 29፣ 2007 ዓ.ም አመታዊ ጉባኤውን በጀርመን አገር አካሄዷል። እንደተለመደው ሁሉ ጉባኤው የተከፈተው በኢሕአፓ የትግል ታሪክ ውስጥ መስዋዕት ለሆኑት ጓዶች የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት በማድረግ ነበር። ከበርካታ የጀርመን ከተሞች የተወከሉ አባላት ተገኝተው በነበሩበት በዚህ ጉባኤ ላይ የስራ አመራር ኮሚቴና የአካባቢ ኮሚቴዎች ሪፖርቶች ቀርበው ወይይት ከተካሄደባቸው በሁዋላ ታይተዋል በተባሉ ድክመቶችና ጉድለቶች ላይ የመፍትሄ ውሳኔዎች የተጠቆሙ ሲሆን፣ ውሳኔዎቹ ሁሉ በቶሎ በስራ ላይ እንዲተረጉሙ ተወስኗል። ፣ በአጠቃላይ ጉባኤው የተካሄደው እንደወትሮው ግልጽ ውይይትና ዴሞክራስያዊ የሀሳብ ፍጭት በሰፈነበት መንፈስ ሲሆን፣ ከመቼውም ግዜ በላቀና በተለየ መልኩ ድርጅቱን የማጠናከር ፍላጎትና ስሜት በአህጽኖት ሲገለጽ የታየበት ስብሰባ ነበር።

በመጨረሻም ጉባኤው የኢሕአፓን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ፣ የትግሉን አካሄድ፣ በወቅቱ ያለውን የሃይል አሰላለፍና የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ በስፋትና በጥልቀት ከመረመረ በሁዋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል። ውሳኔዎቹም፣

- ሁለንተናዊ እንቅስቃሴውን ለማጠናከር ካሁን በፊት የገባውን ቃል ኪዳን በአዲስ መንፈስ አድሶ ትግሉን ይቀጥላል።

- ድርጅታችን አባል በሆነበት ኢዴሃህ አማካኝነት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሰኬታማ እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋጽኦ በአካባቢው ማድረጉን ይቀጥልበታል።

- እብሪተኛውና ዘረኛው የወያኔ\ኢህአዴግ አሸባሪ መንግስት በህዝባችን ላይ የሚፈጽመውን የሰብአዊ መብት ረገጣ፣ በተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባለቶቻቸው ላይ የሚፈጽመውን እስራትና ግድያ፣ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት በመዝረፍ የሚያካሂደውን ተራና ግልጽ የሌብነት ተግባር፣ የኢኮኖሚ እድገት ተገኘ የሚል መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የተሳሳተ መልዕክት የማስተላለፍ ሸፍጥ፣ ህዝባችንን በስራ አጥነትና የኑሮ ውድነት ለመቅጣት የሚደረገው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ፣ የሃይማኖትና የብሄረሰቦች ልዩነቶችን በማራገብ ህዝቡን እርስ በርሱ በማጋጨት በማያቋርጥ የዕልቂትና ስቃይ አዙሪት ውስጥ በማሽከረከር እየተጫወተ ያለውን ሰይጣናዊ ቧልት አጠብቆ ያወግዛል።

- በሶማሊያ ውስጥ የባዕዳንን ተልዕኮ  ለማሟላት እያካሄደው ባለው የጣልቃ ገብ ጦርነት የኢትዮጵያ ልጆች  እንዲማገዱ የሚደረገውን ሕገወጥ እርምጃ በአስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል።
- ሀገር በቀል የሆኑት ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴና በቅርቡ የተቋቋመውን አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አድናቆቱን እየገለጸ ትግላቸው ስኬታማ እንዲሆን ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል።
- ወያኔ\ ኢህአዴግ የተካነበትን የሸፍጥና ውሸት ሙያ መሰረት በማድረግ ፍጹም የማያውቀውንና የማያምንበትን የኢትዮጵያን ታሪክ ከ100 አመት ወደ 2000 አመታት ከፍ በማድረግ፣ < ሚሌንየም> ብሎ በመሰየምና በዓሉ በኢትዮጵያ እንዲከበር ከኢትዮጵያውያን በላይ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ሽር ጉዱን ተያይዞታል። የሚሌንየም የድግስ ፕሮጀክቱ ዋና አላማ የተበላሸውንና በደም የታጠበውን ዘግናኝ የፖለቲካ ገጽታውን የጸዳ አዲስ መልክ እንዲጎናጸፍ ለማድረግ፣ ከበዐሉ ንግድ ገቢ ከሚገኝ የሚሊዮኖች ዶላር ገቢ ምንግዜም በቃኝ የማይለውን የገንዘብ ጥማቱን በትንሹ ቢሆን ለማርካት፣ እየተገባደደ ያለውን አረመኔያዊ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም በመሆኑ፣ ይህ ታውቆ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የወያኔ መጠቀሚያ ከመሆን እንዲጠነቀቁና <ሚሌንየም> በማለት በኢትዮጵያውያን ሬሳ ላይ ዳንኪራ ለመርገጥ የሚደረገውን እሽኮለሌ በጋራ ትግል እንዲከሽፍ ጥሪውን ያስተላልፋል።

- ትውልድን እያጠፋ ያለውን የኤድስ ወረርሽኝ በሽታ ለመከላከል ገዢው መንግስት ተብዬ ክልሌ በሚለው ክፍል የሚያደርገውን ርብርቦሽ፣ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የማስፋፋትና የማዳረስ ሀላፊነት እንዳለበት በአህጽኖት ያሳስባል። በአገርና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሽታውን ለመከላከል እንዲቻል እርዳታቸውን የበሽታው ሰለባ ለሆኑት ምስኪን ወገኖቻችን እንዲለግሱ ይማጸናል።

- በመላው ኢትዮጵያ በወያኔ ታጣቂዎችና በአጋዚ ሰራዊት በከንቱ የፈሰሰው የንጹህ ኢትዮጵያውያን ደም ምላሽ ሳያገኝ፣ በወያኔ እስር ቤት የሚመቅቁት ቁጥራቸው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ እስረኞች ሳይፈቱና በጠመንጃ የተነጠቀው የህዝብ ድምጽ ሳይከበር በየቦታው በሰላም ስም እየተቀነቀነ ያለውን < ዕርቀ ወያኔ ጥሪ > እንዲሁም የቀጣዩን ምርጫ ዝግጅትና ተሳትፎ በጥብቅ ይኮንናል።

- አገራችንን ከስር መስረቷ ንዶ ለመጣል እንቅልፍ ሳይተኛ በሁሉም አቅጣጫ በመራወጥ ላይ ያለውን ጎሰኛ የወያኔ ቡድን እድሜ ለማሳጠር ተቀዋሚ ድርጅቶች በሚያስተባብራቸው መለስተኛ አገራዊ ፕሮግራም ዙሪያ ተሰባስበው ሀቀኛ ህብረት ፈጥረው እንዲታገሉ ጥሪውን ያቀርባል።

ድርጅታዊ ህብረታችን ይጠንክር!!!

ክብርና ሞገስ ለሰመዕቶች!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!